# <u>*የአቶ ሳሙኤል አለማየሁ አስፋዉ አጭር የሕይወት ታሪክ*</u>

አቶ ሳሙኤል ዓለማየሁ አስፋው ከናታቸው ከወይዘሮ እታፈራሁ ኃይለማርያምና ከአባታቸው ከአቶ አለማየሁ አስፋው በደምቢዶሎ ከተማ ሰኔ 5/1934 ዓ/ም አርብ ቀን ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ ተወለዱ። ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስም በአዲስ አበባ የአርበኞች ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከዚያም በንግድ ሥራ ትምህርት ቤት (ኮሜርስ) ተምረው ተመርቀዋል። አባታቸው በሚሩፋቸው የተነሳም አቶ ሳሙኤል የከፍተኛ ትምህርት የመቀጠል ዓላማቸውን አቋርጠው በበስ ኩባንያ በመቀጠር ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን አስተምረዋል፤ አሳድገዋል። በበስ ኩባንያ የሠራተኛ ማህበርም በሃላፊነት አገልግለዋል።

በ1960 ደግሞ ወደ አሜሪካ በመጔዝ በኮርኔል ዩንቨርሲቲ የባችለርና የማስተር ዲግሪአቸውን በኢኮኖሚክስ ቤለበር ሪሌሽንስ አግኝተዋል። አቶ ሳሙኤል አሜሪካ በነበሩበት ጊዜ በተማሪው እንቅስቃሴ ሙሉ ተሳትፎ ከማድረጋቸውም ሌላ በኢሕአፓ እየተጀመረ በነበረው ድርጅታዊ ሥራ አባል በመሆን ተንቀሳቅሰዋል። ከዚያም የድርጅቱን ጥሪ በመቀበል ወደሃገር ተመልሰው በተለይም በሰራተኛ ማህበር አካባቢ ሠርተዋል። በኢሕአፓ ሙሉ አባልነትም በኢንተር ዞን ደረጃ ሃላፊ በመሆን በአዲስ አበባ፤ ሐረርና ወሎ የሠሩት አቶ ሳሙኤል በደርግ ተይዘው ታስረው እንግልት ደርሶባቸው ነበር። ከእስር ሲፈቱ ሕቡዕ በመሆን የቀይ ሽብር ጭፍጨፋ በሚካሄድበት ወቅትም ትግሉን በማስተባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። አቶ ሳሙኤል በገጠርም በትግራይ፤ በጎንደርና ጎጃም በተካሄደው የኢሕአፓ ትጥቅ ትግልም በአመራር ደረጃ ሙሉ ተሳትፎን ያደረጉ ሲሆን ወያኔም ስልጣን ከያዘ በኋላ በሱዳን ትግላቸውን ቀጥለዋል። በዚህ ቦታም አፈሳን ካመለጡ በኋላ በአወሮፓ ወዘተ ይህንኑ ትግል በድንገት እስካረፉበት እስከ ሃሙስ ታኅሳስ 20 ቀን 1998 ዓ/ም ድረስ ቀጥለዋል። የኢሕአፓ ሶስተኛ ጠቅላላ ጉባኤ አቶ ሳሙኤል በኢሕአፓ ትግል ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦና ላሳዩት ቆራጥና ብቁ የአመራር ችሎታቸም የእወቅናና የምስጋና ምስክር ወረቀት ሰጥቷቸዋል።

አቶ ሳሙኤል ዓለማየሁ ለሕዝቡና ለሃገር ሲሉ ለዓመታት መከራን የተቀበሉ፤ ከጔዶቻቸው ጋር ሆነው በጽናትና በጀግንነት የታገሉ፤ ትሁት፣ ታታሪ፣አኩሪ፣ አስተባባሪ፣መካሪ ተማሪም አስተማሪም ነበሩ። ለቤተሰቦቻቸው ፤ ለድርጅታቸው፤ ለሃገራችንም የሚያጎድሉት አቶ ሳሙኤል አንድ ታናሽ ወንድማቸው አቶ ዳዊት በቀይ ሽብር በወሎ የተገደሉ ሲሆን ሁለቱ ሌሎች ወንድሞቻቸው አቶ ዳንኤልና አቶ እያሱ እንዲሁም እህታቸው ወ/ሮ ሐናና ወ/ት ሳባ ከእናታቸው ከወይዘሮ እታፈራሁ ጋር በሕይወት አሉ።አቶ ሳሙኤል በተሰጣቸው ጊዜ ከሚጠበቀው በላይ ለሃገርም ለወገንም ሰርተው አልፈዋል።

ከቤተሰቦቻቸውና ከጔደኞቻቸው